# የACPS Express 8/26/2022: ከትምህርት ቤት የመጀመሪያ ቀናት፣ ጠቋሚ-በሆነው ቪዲዮ - ተደሰቱ!

## ቪዲዮ: የትምህርት ቤት የመጀመሪያ ቀናትን፣ ጠቋሚ-የሆነውን በመመልከት ተደሰቱ!




በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)፣ የ2022-23 የትምህርት ዓመት ተከፍቶ፣ ተማሪዎች ወደ ክፍል - ሰኞ፣ ኦገስት (Aug.) 22 ቀን 2022 ተመልሰዋል። [የመጀመሪያ የትምህርት ቀናቶች የሚያሳየው ቪዲዮአችን]() ከሴፕቴምበር (Sept.) 1 ቀን 2022 ጀምሮ ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (interim superintendent) በመሆን የሚያገለግሉት በዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) እና ሌሎች የክፍል/division መሪዎች ጋር በመሆን፤ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች የጎበኙ እና ተማሪዎችን እና ሠራተኞችን ሠላም-ሲሉ የነበረውን አንዳንድ አስደሳች-ሁኔታዎችን ቀርጾ-የሚያሳይ ነው።

## የማስተማር፣ የመማር እና የአመራርነት መምሪያ (DEPARTMENT OF TEACHING, LEARNING, AND LEADERSHIP)፤ ዶ/ር ፒሬት ፊኒ (Pierrette Finney)ን እንደ - የትምህርት ቤት አመራር-ዋና ዳይሬክተር አድርጎ ተቀብሏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ዶ/ር ፒሬት ፊኒ (Pierrette Finney)ን እንደ - የክፍሉ/division የትምህርት ቤት አመራር - ዋና ዳይሬክተር ሆነው መመረጣቸውን ሲያሳውቅ-ደስታ ተሰምቶታል። ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney)፣ ከ2015 ጀምሮ እንደ የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት (FCH) - ርዕሰ መምህር፣ እና እንደ የርዕሰ-መምህር መሪ ሆነው ለአለፉት ሁለት ዓመታት

አገልግለዋል። ከዚህ-ቀደም፤ የጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት - የቀለም-ትምህርት ርዕሰ መምህር እና ርዕሰ መምህር ሆነው፤ እንዲሁም በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት - እንደ የቀለም-ትምህርት ርዕሰ መምህር እና የቀለም-ትምህርት ርዕሰ መምህር ዋና መሪ ሆነው አገልግለዋል። በተጨማሪም - ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney)፣ እንደ ከK-12 እና የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት አስተማሪነት፤ የበርካታ-ዓመታት ልምድ አላቸው።

በACPS አመራርነት ቡድን ውስጥ በሚኖራቸው አዲስ የስራ-ድርሻ፤ ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney) - በሙያ-ስልጠና መማር፣ የዋጋ አመራር ማሰልጠኛ እና ስልጠና አሰጣጥ፣ እንዲሁም የተቀናጀ የማህበረሰብ ልምድ እና ደረጃውን-የጠበቀ የክንውን ሂደት በትምህርት ቤቶች ዙሪያ እና በአመራር ቡድኖች ዙሪያ መኖሩን በማረጋገጥ ላይ፤ ከትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ጋር በቀበት-ይሠራሉ። እንደ የረጅም-ጊዜ ትምህርት-ሰጪነታቸው፤ ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney) - በACPS ትምህርት ቤቶች ላይ ያላቸውን ጥልቅ-የሆነ እውቀታቸውን እና በትምህርት ቤት አመራርነት እና ከPreK-12 እና ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ላይ ያላቸውን ሰፊ-ልምድ ወደ አዲሱ የስራ-ድርሻቸው የሚያመጡ ይሆናል።

“ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney)ን ለሰጡት የአመራርነት ብቃት እና በFCH ውስጥ ለተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ላሳዩት ቁርጠኝነት ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney) ያላቸውን የብቃት-ደረጃ በማስፋት - ሁሉንም በትምህርት ቤት ክፍላችን/division የሚገኙ ተማሪዎችን ለማገልገል በመቻላቸው እድለኞች ነን፤” ብለዋል - ዶ/ር ዌንዲ ጎንዛለዝ (Dr. Wendy Gonzalez) - የACPS የማስተማር፣ የመማር እና የአመራርነት ሹም (Chief of Teaching, Learning, and Leadership)።

ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney) - የባችለር ሣይንስ ዲግሪ በባዮሎጂ ከሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ (University of Maryland Eastern Shore) ያላቸው፣ የማስተርስ ዲግሪ - በትምህርታዊ አመራር - ከጆርጅ-ሜሰን ዩኒቨርስቲ፣ እና ሁሉን-ምድቦች ያካተተ የልዩ ትምህርት ከሬጌንት ዩኒቨርስቲ (Regent University)፣ እንዲሁም የዶክተሪያል ዲግሪ በትምህርታዎ አመራር - ከሊበርቲ ዩኒቨርስቲ (Liberty University) የያዙ-ናቸው።

ዶ/ር ፊኒ (Dr. Finney) አዲሱን የአመራርነት የስራ-ድርሻቸውን ሲወስዱ፤ አኒካ ቡስተር-ሲንግለቶን (Anika Buster-Singleton) - የ‘FCH’ እንደ ተጠባባቂ ርዕሰ መምህር እና ‘Quanda Fudd’ ተጠባባቂ የቀለም-ትምህርት ርዕሰ መምህር - ሆነው ያገለግላሉ።

## የማስተማር፣ የመማር እና የአመራርነት መምሪያ (DEPARTMENT OF TEACHING, LEARNING, AND LEADERSHIP)፤ ካርሜን ሳንደርስ (Carmen Sanders)ን እንደ - የትምህርት-አሰጣጥ እርዳታ - ዋና ዳይሬክተር አድርጎ ተቀብሏል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ካርሜን ሳንደርስ (Carmen Sanders)ን እንደ የትምህርት-አሰጣጥ እርዳታ፣ ዋና ዳይሬክተር ሆነው መመረጣቸውን ሲያስታወቅ-ደስታ ይሰማዋል። በአሁኑ-ጊዜ፣ ለአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School)- ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) - (ACHS)፤ የካምፓስ አስተዳዳሪ ሆነው፣ ከ2019 ጀምሮ ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከዚህ-ቀደም፤ ሚስ ሳንደርስ (Ms. Sanders)፣ የጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት (GW) - ረዳት ርዕሰ መምህር፤ እና በACHS - የተማሪዎች ዲን (dean) ነበሩ። የትምህርታዊ-የስራ መስክን በ2006 ጀምሮ ያጀመሩ እና፣ እንደ አስተማሪ በመማሪያ-ክፍል ውስጥ እስከ 2012 ድረስ አገልግለዋል።

“ለቲታኖቻችን (Titans) ላደረጉት አመራር እና ቁርጠኝነት - ሚስ ሳንደርስ (Ms. Sanders)ን ላመሰግናቸው እወዳለሁ፤ እና አዲሱን የስራ-ድራሻቸውን በACPS ውስጥ በሚጀምሩበት ጊዜ፣ መልካሙን-ሁሉ እመኝላቸዋለሁ። ሚስ ሳንደርስ (Ms. Sanders) - ተማሪዎቻችንን በመርዳት እና ሠራተኞች በመማር እንዲሁም በዚህ-በጣም ፈታኝ-በሆኑ ዓመታት ውስጥ በጤናማነት በመቆየት እንዲገፉ - ወሳኝ-የሆኑ ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል፤” ብለዋል ፒተር ባላስ (Peter Balas) - የACHS ዋና ርዕሰ መምህር።

በአዲሱ የአመራርነት የስራ-ድርሻ፤ ሚስ ሳንደርስ (Ms. Sanders) - እንደ የመማር እና የአመራርነት መምሪያ (Department of Teaching, Learning and Leadership) አባል-በመሆን፤  ለሁሉም በACPS ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ የትምህርት አሰጣጥ አመራርነትን እና እርዳታን ይሰጣሉ።
“እንደ ሚስ ሳንደርስ (Ms. Sanders) ያለ የሙያ-ብቃት እና የዓመታት ልምድ በACHS እና GW ያለው፣ እንደ አዲስ የትምህርት-አሰጣጥ እርዳታ-ሰጪ ዋና ዳይሬክተር ሆነው፤ ሁሉንም በትምህርት ቤት ክፍላችን/division ውስጥ ለማገልገል የሚችል ሰው በማግኘታችሁ ደስተኞች ነን፣” ብለዋል ዶ/ር ዌንዲ ጎንዛለዝ (Dr. Wendy Gonzalez) - የACPS የማስተማር፣ የመማር እና የአመራርነት ሹም (chief of teaching, learning and leadership)።

ሚስ ሳንደርስ (Ms. Sanders) - የባችለር ዲግሪ በእንግሊዘኛ-ቋንቋ፣ በ‘literature and composition’፣ ከቨርጅኒያ ፖሊቴክኒክ ዩኒቨርስቲ (Virginia Polytechnic University)፣ እና የማስተርስ ዲግሪ በትምህርታዊ አስተዳድር - ከትሪኒቲ ዩኒቨርስቲ (Trinity University) የያዙ ናቸው።

ይህን አዲስ የአመራርነት የስራ-ድርሻን ሚስ ሳንደርስ (Ms. Sanders) በሚወስዱ ጊዜ፤ ክርስተፈር ስፒች (Christopher Speich) - እንደ የACHS-King Street ተጠባባቂ የካምፓስ አስተዳደር መሪ ሆነው፣ እና ኦሊንካ ተርነር (Olinka Turner) - በልዩ-ሁኔታ የሚሰጥ (Specialized) የትምህርት አሰጣጥ - ተጠባባቂ የአስተዳደር መሪ ሆነው ያገለግላሉ።

## የ‘Back to School’ ቅጾችን ሞልታችሁ-በማጠናቀቅ፤ የተማሪ ደህንነትን በማረጋገጥ፣ እባካችሁ እርዱ



የ‘Back to School’ መረጃ ማረጋገጫን - በ‘PowerSchool’ ውስጥ ወይም የታተመውን ጥራዝ ሞልቶ-በማጠናቀቅ ማረጋገጫውን-መስጠት፤ አስፈላጊ-በሚሆን ጊዜ ቤተሰቦችን ለማግኘት መቻሉን ለማረጋገጥ የሚረዳን በጣም-ጠቃሚ የሆነ ወሳኝ-ነገር ነው። የተማሪውን የአስቸኳይ የአደጋ-ጊዜ (emergency) የሚገኝ-ሰው መረጃ፣ እና የጤና መረጃን መስጠት፤ ለአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)ን ተማሪዎችን በመርዳት-ላይ፤ አሁንም-ቢሆን ሌላ የደህንነት ጥበቃ እርምጃ መውሰጃ መንገድ ሆኖ የሚረዳው ነው። ይህ መረጃ በአሁኑ-ጊዜ የምትጠቀሙበትን መገኛ-አድራሻ ተስተካክሎ የያዘ መሆኑን ማረጋገጥ እንፈልጋለን፤ ይህም - በጤና፣ ደህንነት እና የጥበቃ-ጉዳዮች በሚያጋጥሙ ጊዜ ቤተሰቦችን ለማግኘት ስለሚረዳን ነው።

ከዚህ-ቀደም ከነበረው ዓመት ምንም-ለውጦች ባይኖርም እንኳን፤ ሁሉም የ‘Back to School’ ቅጾች፤ ለእያንዳንዱ ልጅ እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 ድረስ-ተሞልቶ መጠናቀቅ አለበት። ምንም የጤና እና የአስቸኳይ የአደጋ-ጊዜ የሚገኝ-ሰው (emergency contact) መረጃዎች ለውጦች አለመኖራቸውን እያንዳንዱ-ቤተሰብ ማረጋገጡ፤ እኛም ሁሉም መረጃዎች የተስተካከሉ መሆናቸውን ለማወቅ ይረዳናል።

የ'Back to School’ ቅጾችን አጠናቅቆ-ለመሙላት ቀላሉ-መንገድ፤ በኦንላይን ቅጾቹን በማግኘት ይሆናል። የ‘PowerSchool Parent Access’፣ የኦንላይን ፖርታል (online portal) ሲሆን፤ የልጅዎን የመገኛ-አድራሻ (contact) እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ለማስተካከል (update ለማድረግ) የሚችሉበት ቦታ ነው። ማድረግ-የሚገባችሁ፤ አንድ የመግቢያ (login) እና የመግቢያ-ኮድ (password) ብቻ ሲሆን፤ የልጅዎን የጊዜ-ሰሌዳ፣ በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) መዝገብን፣ ያሳዩትን የእድገት-ሂደት፣ የውጤት-ደረጃዎች እና የ‘standardized assessments’ን ማየት ትችላላሁ። ይህ የኦንላይን ፖርታል፤ በተጨማሪም - የልጅዎን የምሣ ፒን (PIN)፣ የአስተማሪ ኢሜል አድራሻዎች እና ሌሎች ቤተሰቦች ከተማሪያቸው ትምህርት ጋር የሚያገናኟቸውን ጠቃሚ-የሆኑ መረጃዎችን ማግኛ-ዘዴም ነው።

እንግሊዘኛ- እና ስፓኒሽ-ተናጋሪ ቤተሰቦች - ከኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ (electronic device) ጋር፤ አስፈላጊ የሆኑትን ቅጾች በ‘PowerSchool’ ውስጥ ለመሙላት - ከዚህ በታች-ያለውን ማገናኛዎች (links) መጠቀም አለባቸው:

- እንግሊዘኛ/English 2022-23 የ‘Back to School’ ቅጾች።
- ስፓኒሽ/Spanish 2022-23 የ‘Back to School’ ቅጾች።

በ‘PowerSchool’ ላይ የአሳዳጊ አካውንትን ለመፍጠር እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ የመመሪያ-ትዕዛዝ ቪዲዮ፤ በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ ይገኛል።

በተጨማሪም፤ የአማርኛ- እና የአረብኛ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች - የታተመ የ‘Back to School’ ጥራዝ (packet)ን ከልጆቻቸው ትምህርት ቤቶች ለማግኘት እንዲጠይቁ፤ ወይም አማርኛ እና አረብኛ ቅጾችን በኦንላይን ላይ በማግኘት እንዲሞሉ፤ እናበረታታቸዋለን። እንግሊዘኛ- እና ስፓኒሽ-ተናጋሪ ቤተሰቦች - የኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ-የሌላቸው (without an electronic device)፤ እነርሱም የታተመ ጥራዝ (packet)ን ከትምህርት ቤቶቻቸው ለማግኘት መጠየቅ፤ ወይም እንግሊዘኛ እና ስፓኒሽ ቅጾችን በኦንላይን ላይ በማግኘት ሊሞሉም ይችላሉ። ተሞልተው-የተጠናቀቁ የታተሙ ቅጾች፤ ወደ ትምህርት ቤቱ የእንግዳ-መቀበያ ቢሮ (front office) እስከ ሴፕቴምበር (September) 30 ቀን 2022 ድረስ፣ መግባት-አለባቸው።

## ለሴፕቴምበር (September) ወር የሚከናወኑ: የማህበረሰብ ተሣትፎ እና የቀን-መቁጠሪያ (Calendar) ማስታወሻዎች

Community Outreach & CALENDAR REMINDERS

ከዚህ ዕትም-ጀምሮ፤ የ*ACPS Express* እና የ*ACPS Insider*፤ ወርሃዊ የቀን-መቁጠሪያ (Calendar) ማስታወሻዎችን እና፣ ወደፊት-የሚከናወኑ የማህበረሰብ ዝግጅቶችን - የሚገልጽ-ይሆናል። የACPS የማህበረሰብ ሁሉን-የሚያዳርስ (Community Outreach) ቡድን፤ በእናንተ አጎራባች-አካባቢ - መቼ እንደሚገኙ እወቁ!

**የ'UNCUT' ታዳጊ የ'Back to School' የማህበረሰብ-ቀን (Community Day)**
ቅዳሜ፣ ኦገስት (Aug.) 27 ቀን 2022፤ ከ12-4 p.m.
በOld Towne Pool (1609 Cameron St.)

UNCUT Youth፤ የታዳጊዎች ኃይልን-መስጫ እና መካሪ-የሆነ ድርጅት (youth empowerment and mentoring organization)፤ የማህበረሰብ ቀን (community day)ን፣ ከጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston)) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት አጠገብ በሚገኘው መንገድ ላይ ያዘጋጃል። 'UNCUT Youth'፣ ነፃ የትምህርት ቤት ቁሳቁሶች (school supplies) እና ፀጉር መቁረጥን የሚሰጥ እና፣ ቤተሰቦች ምግብ እና አስደሳች-የሆኑ እንቅስቃሴዎችን - እንደ ዋና-መዋኘት፣ ጌሞች (games)፣ moon bounce እና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን በማግኘት መደሰት ይችላሉ።

**የ'Labor Day' በዓል**
አርብ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 2 ቀን 2022

ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች፣ በ'Labor Day' በዓል ምክንያት ዝግ-ይሆናሉ።

**የ'Labor Day' በዓል**
ሰኞ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 5 ቀን 2022

ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች፤ በ'Labor Day' በዓል ምክንያት ዝግ-ይሆናሉ።

**የ'Back To School' ምሽት: መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤቶች**
ሮብ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 7 ቀን 2022

የ'Back To School' ምሽት፤ ቤተሰቦች - ስለ ልጆቻቸው አስተማሪዎች እና የዚህ ዓመት ክፍሎቻቸው የበለጠ ለማወቅ የሚያስችላቸው ግሩም-የሆነ ዕድል ነው። በጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት እና በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች፤ እንዲካፈሉ ተጋብዘዋል።

**የ‘Back To School’ ምሽት: የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) - ሁሉም ካምፓሶች**

የ‘Back To School’ ምሽት (Back to School Night (BTSN)፤ ቤተሰቦች - ስለ ልጆቻቸው አስተማሪዎች እና የዚህ ዓመት ክፍሎቻቸው የበለጠ ለማወቅ የሚያስችላቸው ግሩም-የሆነ ዕድል (BTSN) ነው። የግንባታ-ስራዎች እና የጥገና ፕሮጀክቶች ባስከተሉት የመኪና ማቆሚያ ችግር ምክንያት፤ የACHS - ኪንግ ስትሪት (King Street) እና ሚኒ ሃዋርድ (Minnie Howard) ካምፓሶች - የ‘Back To School’ ምሽት እንቅስቃሴዎችን - **በርቀት (virtually)** የሚያካሂዱ እንደሆኑን፣ እባካችሁ አስታውሱ። በርቀት (virtual) የ‘BTSN’ አቀማመጥ ውስጥ፤ አስተማሪዎች በቅድሚያ-የተቀዱ ቪዲዮዎችን ያዘጋጁ እና በካንቫስ (Canvas) አማካኝነት - 6 p.m. ከማለፉ-በፊት የሚያጋሩ-ይሆናል። ከ‘BTSN’ ዝግጅቱ በፊት፣ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎችን፣ ሠራተኞች ያጋራሉ።

- ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) - **በርቀት (Virtual)**: ቪዲዮዎች፤ በካንቫስ (Canvas) አማካኝነት ሐሙስ፤ ሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን፤ 6:00pm ከማለፉ-በፊት፣ የሚጋሩ-ይሆናል።
- ሚኒ ሃዋርድ ካምፓስ (Minnie Howard Campus) - **በርቀት (Virtual)**: ቪዲዮዎች፤ በካንቫስ (Canvas) አማካኝነት ሮብ፤ ሴፕቴምበር (Sept.) 7 ቀን፤ 6:00pm ከማለፉ-በፊት፣ የሚጋሩ-ይሆናል።
- ቻንስ ፎር ቼንጅ ካምፓስ (Chance for Change Campus): **በአካል-ተገኝቶ** የሚካሄድ ‘BTSN’ አቀማመጥ፤ ሮብ፤ ሴፕቴምበር (Sept.) 7 ቀን፣ በ6 p.m
- ሳተላይት ካምፓስ (Satellite Campus): **በአካል-ተገኝቶ** የሚካሄድ ‘BTSN’ አቀማመጥ፤ ሮብ፤ ሴፕቴምበር (Sept.) 7 ቀን፣ በ6 p.m

**ALIVE! ‘Pop-Up’ የምግብ ማከፋፈያ (Food Distribution)**
ሐሙስ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022፤ ከ4:30 p.m. - 6:00 p.m.
በ‘William Ramsay Recreation Center’ (5650 Sanger Ave.)

ALIVE!፤ የአካባቢው ለትርፍ-የማይሰራ ድርጅት (not-for-profit organization) ሲሆን፤ በድህንነት ለሚኖሩ የተራቡ - በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ የሚገኙ - ልጆች፣ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች፣ የአስቸኳይ-ጊዜ እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን በመስጠት በትጋት የሚሠራ ነው። ALIVE! ለአሌክሳንድርያ ከተማ ነዋሪዎች - በዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመዝናኛ ማዕከል - የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ፣ የምግብ ጥቅሎች (bags of food) ያከፋፍላል። ምንም፣ መታወቂያ (ID) አያስፈልግም።

**ALIVE! ‘Pop-Up’ የምግብ ማከፋፈያ (Food Distribution)**
አርብ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 9 ቀን 2022፤ ከ4:30 p.m. - 6:00 p.m.
በ‘Casa Chirilagua’ (4109 Mt. Vernon Ave.)

ALIVE!፤ የአካባቢው ለትርፍ-የማይሰራ ድርጅት (not-for-profit organization) ሲሆን፤ በድህንነት ለሚኖሩ የተራቡ - በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ የሚገኙ - ልጆች፣ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች፣ የአስቸኳይ-ጊዜ እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን በመስጠት በትጋት የሚሠራ ነው። ALIVE! ለአሌክሳንድርያ ከተማ ነዋሪዎች - በ‘ካሳ ቺሪላጉዋ (Casa Chirilagua)’ - የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ፣ የምግብ ጥቅሎች (bags of food) ያከፋፍላል። ምንም፣ መታወቂያ (ID) አያስፈልግም።

**የ‘Back To School’ ምሽት: የመጀመሪያ-ደረጃ & ከK-8 ትምህርት ቤቶች**
ሐሙስ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 15 ቀን 2022
በጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson-Houston) ከPreK-8፣ ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከK-8 እና ሁሉም የመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የ‘Back-To-School’ ምሽት፤ ቤተሰቦች - ስለ ልጆቻቸው አስተማሪዎች እና የዚህ ዓመት ክፍሎቻቸው የበለጠ ለማወቅ የሚያስችላቸው ግሩም-የሆነ ዕድል ነው። ለተጨማሪ ዝርዝር መግለጫዎች ለማግኘት፤ እባካችሁን የትምህርት ቤታችሁ ድህረ-ገጽ ተመልከቱ።

**የ‘Rosh Hashanah’ በዓል**
ሰኞ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 26 ቀን 2022

ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች፣ በ‘Rosh Hashanah’ በዓል ምክንያት ዝግ-ይሆናሉ።

**የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት & የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች**
ሐሙስ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 29 ቀን 2022

የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለቤተሰቦች እና አስተማሪዎች፣ ስለ ተማሪው የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የመማር ላይ - ስለሚያሳየው እድገት ለመወያየት፤ በጣም ጠቃሚ-የሆነ እዕድልን የሚሰጥ ነው። ስለ ኮንፈረንሶቹ የጊዜ ሰሌዳን በተመለከተ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል።

**የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት & የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች**
አርብ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022

የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለቤተሰቦች እና አስተማሪዎች፣ ስለ ተማሪው የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የመማር ላይ - ስለሚያሳየው እድገት ለመወያየት፤ በጣም ጠቃሚ-የሆነ እዕድልን የሚሰጥ ነው። ስለ ኮንፈረንሶቹ የጊዜ ሰሌዳን በተመለከተ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል።

**የ‘Back to School’ ቅጾችን ማጠናቀቂያ - የሚያበቃበት የጊዜ ገደብ**
አርብ፣ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022

እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 ድረስ፣ ሁሉም ቤተሰቦች የ‘Back to School’ ቅጾችን ለተማሪዎቻቸው ተሞልቶ-መጠናቀቁን እርግጠኛ መሆን-ያስፈልጋቸዋል። በአደጋ-ጊዜ መገኘት የሚችሉ ሰዎች አድራሻዎችን፣ የልጆችን የጤና መረጃዎች እና በማንኛውም የመውጣት (opt-out የማድረግ) ምርጫዎችን በመግለጽ፣ ከሌሎች-በእነዚህ ጥራዞች ውስጥ ጠቃሚ-የሆኑ ነገሮች ጋር፤ እባካችሁ ቤተሰቦች-እንድታረጋግጡልን እንጠይቃለን።

## ACPS - ብቁ-የሆኑ የአውቶቡስ ሹፌሮችን ለመቅጠር ሲባል - አዲስ የገንዘብ-ማግኛ ማበረታቻ (Financial Incentive)ን፣ አቅርቧል



በሃገሪቱ ዙሪያ፣ ብቁ-የሆኑ የአውቶቡስ ሹፌሮችን ለመቅጠር ባለው ከፍተኛ-ተፈላጊነት፤ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ለአዲስ-ተቀጣሪዎች፣ ለትምህርት ቤት ክፍል/division የሙሉ-ሰዓት (full-time) የአውቶቡስ ሹፌሮች፤ የመቅጠሪያ የገንዘብ ማበረታቻን አቅርቧል።  ይህ ማበረታቻ፣ የመጓጓዣ አገልግሎት አመልካቾችን እና አዲስ ተቀጣሪዎችን መጠን-ለማሳደግ ይረዳል።

የሙሉ-ሠዓት (Full-time)፣ ለACPS አዲስ የአውቶቡስ ሹፌር ተቀጣሪ-ለሆኑ፣ የ$3,000 የማበረታቻ-ክፍያ (incentive) ያገኛሉ። ገንዘቡ፣ በሁለት የተለያየ-አከፋፈል የተሰበጣጠረ ይሆናል:

- $1,500 በቅጥር-ጊዜ የሚቀበሉት።
- በጃንዋሪ (January 2023) የሚቀበሉት $1,500

ACPS፤ ተማሪዎች - በወጣው የጊዜ-ሰሌዳ የመሄጃ-መንገዶች በየቀኑ፣ እንዲሁም በልዩ ዝግጅቶች ቀን፣ እንዲያጓጉዙ፣ ብቁ-የሆኑ የአውቶቡስ ሹፌሮችን ለመቅጠር ይፈልጋል። ሹፌሮቻችን፤ ተሽከርካሪዎችን ደህንነቱ-በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከራቸውን እና ተማሪዎችን በሚያመላልሱበት ጊዜ፣ ወደ አውቶቡሱ በሚጭኑ እና በሚያወጹ ጊዜ፣ የተማሪዎችን ደህንነት መጠበቁን ያረጋግጣሉ።

ከሌሎች የስራ-ኃላፊነቶች ጋር፣ የአውቶቡስ ሹፌሮች የሚከተሉትን ያከናውናሉ:

- የጊዜ ሰሌዳ ባላቸው የመሄጃ መንገዶች ላይ፣ ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት፣ እና/ወይም ከመስክ-ጉዞዎች (field trips) - የመጓጓዣ-አገልግሎት ተሳፋሪዎችን በደህንነት እና ጊዜውን በጠበቀ-ሁኔታ ያጓጉዛሉ።
- በተሳፈሩበት ጊዜ ውስጥ፣ የተማሪዎችን እና የተሳፋሪዎችን ደህንነት መጠበቅ እና የዲስትሪክት ፖሊሲን በመከተል ይቆጣጠራሉ።
- የጉዞ-በፊት እና ከጉዞ-በኋላ ያሉ ምርመራዎች/inspectionsን ያከናውናሉ (ለምሳሌ: የፈሻሽ-መጠኑን፣ የጎማ ንፋስ፣ የውጪ የመኪናውን አካል-ሁኔታ፣ መመልከቻ መስታወቶችን... ወዘተ) የተሽከርካሪውን በደህንነት የመንቀሳቀስ ሁኔታን ለማረጋገጥ፣ እና በግዳጅ-መከተል ያሉባቸውን መመሪያዎች ተገገር በመሆን ያከናውናሉ።
- ተገቢ-የሆኑ-ባህሪያቶች ደንቦችን በማስጠበቅ እና የተሳፋሪዎችን ደህንነት በመጠበቅ፤ ተማሪዎችን እና ሌሎች ተሳፋሪዎችን ያሳስባሉ።

ብቁ-የሆኑ አመልካቾች የሚከተሉት ሊኖራቸው ይገባል:

- ትምህርት (Education): የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ፣ ወይም ከዚያ-ጋር ተመጣጣኝ የሚመረጥ ነው፣ ነገር ግን አስፈላጊ-አይደለም።
- ልምድ (Experience): የስራ-ጋር ግንኙነት ያለው የስራ-ልምድ - ቢኖር-የሚወደድ ነው። ጥሩ-የሆነ - የስራ የቀድሞ-ታሪክ እና የመኪና-መንዳት መዝገብ፣ ያስፈልጋል።
- ሰርቲፊኬቶች እና ፈቃዶች (በACPS የስልጠና ፕሮግራም አማካኝነት የተገኘ ሊሆን ይችላል):
    - ሕጋዊ የClass “B” የንግድ የመንጃ ፈቃድ ለተጓዝ-ተሳፋሪዎች እና ለትምህርት ቤት አውቶቡሽ የሚደግፍ-ሆኖ የተሰጠ።
    - CDL 3ኛ ወገን መርማሪ/examiner (DMV)።
    - ‘CPR/First Aid ሰርተፊኬት’ ቢኖር የሚመከር-ነው።
    - SET (State Efficient Transport) ሰርተፊኬት - የባህሪይ ጣልቃ-ገብነት ስልጠና (Behavior Intervention Training)።

ACPS፤ እየተከፈላቸው የስልጠና-ፕሮግራምን - የንግድ የመኪና መንጃ ፈቃድ (commercial driver’s license (CDL) ሰርትፊኬትን የሚያስገኝ ስልጠና ይሰጠል።

ችግር-እንደሌለ ማጣሪያ (Clearances):

- የወጀል ፍትህ የጣት-አሻራ (Criminal Justice Fingerprint)/ያለፈ-ማንነትን ከአደገኛ-ሁኔታ ነፃ መሆንን (Background Clearance)።
- የሳንባ-ነቀርሳ (Tuberculosis) በቆዳ-ላይ የሚደርግ ምርመራ።

የሕዝብ ጤናን የተከተለ-መሆን

- የ‘COVID’ ክትባቶች መወሰዳቸው ማረጋገጫ። በሃይማኖት/በሕክምና ምክንያት ላለመከተብ-የተደረገ-ከሆን ይታያል።
- የደህንነት እና የጤና ፕሮቶኮሎችን መከተል ያለበት።

የትምህርት ቤት ክፍል/division፤ ግሩም-የሆነ የፕሮግራም ጥቅማ-ጥቅሞችን፤ የጤና ኢንሹራንስ፣ እና የቨርጅኒያ የጡረታ ዘዴን ጨምሮ፤ ለሙሉ-ሰዓት ተቀጣሪ ሠራተኞች ይሠጣል።

ለACPS የአውቶቡስ ሹፌር የስራ-መስኮች፣ ማመልከቻዎችን በኦንላይን ላይ ሞልቶ ማስገባት ይቻላል።

## የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ - ለኦገስት (Aug.) 25 ቀን 2022



በኦገስት (Aug.) 25 ቀን 2022 የትምህርት ቤት ቦርድ - የስራ ክፍለ-ጊዜ (Work Session)፣ የACPS 'Areas of Focus' - ለትምህርት ዓመት 2022-23 ረቂቁን ያካተተ ሲሆን፤ የተማሪ ማህበራዊ/ስሜታዊነት ጠቋሚዎች፣ የእውቅና መስጫ ምክንያቶችን እና የተማሪ ዕድገትን የሚለኩትን - በፌደራላዊ ሁኔታ የተስተካከለ 'Standards of Learning (SOL)' ውጤቶች፣ ስር-የሰደደ ከትምህርት ገበታ መቅረቶች (chronic absenteeism) መጠኖችን፣ እና ቀደምት-ደረጃ ላይ ያለ የትምህርት ቤት እውቅና-መስጠት ሁኔታዎችን ያከተተ ነው።

ACPS፤ በርካታ የሆኑ እርምጃዎችን በቦታው በማስቀመጥ - ለማሪዎችን ለመርዳት እና ከወረርሽኙ እንደገና-የመነሳሳት ጥረቶቹ እንዲቀጥል ትምህርታቸውን ወደፊት-እንዲያራምዱ፤ የ2025 Equity for All Strategic Plan: የበጀት ዓመት 2023 የበጀት ቀድሚያ-የሚሰጥባቸውን፣ የ2022-23 'Areas of Focus'፣ የጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ግምገማ እና ሁሉም ትምህርት ቤት እና መምሪያ ዕቅዶችን ማሻሻልን አካትቶ በስልታዊ-ሁኔታ ጎን-ለጎን ሆኖ የሚከተል ይሆናል። ይህ ጎን-ለጎን ሆኖ አብሮ መጓዝ፤ የትምህርት ቤት ክፍልን ዕቅድ-አወጣጥ እና እርምጃዎች ዒላማ-ያላቸው እና ምላሽ-ሰጪ የመረጃ-ስብስብ (data)ን፤ ቀጣይነት-ባለው ከፍተኛ ተጽዕኖዎችን እና ልዩነቶችን ለሂስፓኒክ እና ጥቁር ተማሪዎች እንዲሁም ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (students with disabilities) ላይ በማሳየት የቀጠለውን እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals)ን እንዲያገኙ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ማግኘታቸው ላይ ይጠቀማል።

የትምህርት ቤት ቦርዱ፤ የዚህን ዓመት የ'Areas of Focus' በሴፕቴምበር (September) ወር ውስጥ በሚያረጋግጥ ጊዜ፤ ትምህርት ቤቶች፣ መመሪያዎች የማሻሻያ ዕቅዳቸውን የሚያጠናቅቁ፣ የዚህን ዓመት የ'Graduation Task Force' የሚያሳውቁ፣ የትምህርት ቤት በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) ለማሻሻል የሚሰሩ እና ሁሉም ተማሪዎች በየቀኑ የ30-ደቂቃዎች የማህበራዊ-ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት (social-emotional and academic learning (SEAL) ጊዜ እንዳገኑ ያረጋግጣሉ። ከK-4 በማንበብና መፃፍ (literacy) ላይ ትኩረት በማድረግ፤ ዋና የድምጽ-አወጣጥ (core phonics) ትምህርት-አሰጣጥን ማሳደግ፣ ከፍተኛ-ጥራት ያለው የ'Tier 1' የትምህርት-አሰጣጥን በቀጣይነት በማቅረብ ማሻሻል፣ እና የትምህርት-ሰጪን የችሎታ-አቅም - የግምገማ ፕሮቶኮሎችን በመለየት፣ ለወሳኝ-የሆኑ መሠረታዊ የማንበብና መፃፍ ችሎታዎችን መገንባትን ያካተተ ይሆናል። በስራ-ክፍለ ጊዜ (Work Session) ላይ የቀረበው የረቂቅ ትኩረት-የተደረገባቸው ዘርፎች - የሚያካትቱት:

- ማህበራዊ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) መልሶ-ማነሳሻ።
- ሂስፓኒክ ወንዶች/Hispanic Males።
- የሠራተኛ ጤናማነት እና እድገት

- የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት - የጤናማነት ተሞክሮ።
- ቅድመ-ኮሌጅ/Early College።
- ተሰጥዖ እና ስጦታ ያላቸው።

ለአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) በ2021 እና በ2022 መካከል - በፌደራላዊ-ሁኔታ የተስተካከለው የ'SOL' ውጤቶች እንደሚያሳዩት፤ ሁሉም ተማሪዎች - ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (students with disabilities) በስተቀረ - በንባብ፣ ሂሳብ፣ እና ሣይንስ እድገትን እንዳሳዩ ያሳየ ሲሆን፤ ቀጣይነት ካለ የCOVID-19 ወረርሽኝ ትጽዕኖዎች ጋር - ብዙዎች በሂሳብ ውጤቶች እና በታሪካዊነት በአነስተኛ-ሁኔታ አገልግሎትን የሚያገኙ (underserved) የተማሪ ቁጥሮችን ላይ በይበልጥ ተጽዕኖ ፈጥሯል። የ2021-22 የጽሁፍ እና የታሪክ (History)/ሣይንስ ውጤቶች፤ ለACPS እንደ ዋና-መነሻ መሠረት ዓመት (baseline year) ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን፤ በ2022 ያለው ተሳትፎ በ30% በተለመደ የተማሪ ቁጥር ግምገማ-በተደረገ ጊዜ ያነሰ-የነበር እና ከቀድሞ ዓመታት ጋር ሊነፃጸር የሚገባው አይደለም። ለአብዛኞዎቹ የተማሪ ንዑስ-ቡድኖች (subgroups)፤ በ2019 እና በ2021 ስር-የሰደደ በትምህርት-ገበታ አለመገኘት ደረጃዎች - እጥፍ-በሚጠጋ ሁኔታ እና ከዚያም-በላይ የነበረ፣ እና በ2022 ከፍ-ብሎ ቆይቷል። ቀደምት-የሆኑ ውጤቶች እንደሚያሳዩት፤ ከ17 የACPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ አስራ-ሦስቱ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት እውቅና-ያገኙ (accredited) እና አራቱ፤ ከሁኔታዎች ጋር እውቅና-ያገኙ (accredited) ናቸው፤ (ፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston)) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት እና አሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

## በኦገስት (Aug.) 18 ቀን 2022 - የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት ደረጃ




እስከ ኦገስት (Aug.) 18 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - መካከለኛ ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 222.0 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።